# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ከተከላካይነት ለመውጣት፥ የአምባ-ገነኖችን ግፍ ለመቋቋም!

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአምባ-ገነኖችን የአገዛዝ አዙሪትና ልዩነትን አሸቀንጥሮ በመጣል የራሱ ዕድል ወሳኝ ሊሆን እንደሚችል በግንቦት ሰባት ቀን ዘጠና ሰባት ዓ/ም ታሪካዊ ምርጫ አስመስክሯል፡፡ ከዚህ አዲስ ምዕራፍ-ከፋች እንቅስቃሴ በተያያዘም የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ንፁኃን ዜጎችን በግፍ እንደጨፈጨፈ፥ በየማጎሪያ ጣቢያው በጅምላ አስሮ እንዳሰቃየ፥ አካለ ጎደሎ እንዳደረገና እንዳንገላታ፥ ከኑሮአቸው እንዳፈናቀለ፥ እንዳሰደደና የብዙዎችን መዳረሻ እንዳጠፋም  ይታወቃል፡፡

ሕዝብ አመኔታውን የጣለባቸውን ተወካዮቹንና ለአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሠረታዊ የሆኑ ተቋማት መሪዎችን በፈጠራ የወንጀል ክስ ሲያንገላታና ሲያሰቃይ ቆይቶ እነሆ ዛሬ ሰኔ ፬ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም የአቶ መለስ ዜናዊ ሕወኃት/ኢሕአዴግን ትዕዛዝ ፈጻሚ የሆነው የካድሬ ዳኞች “ፍርድ ቤት” ተከሳሾች በተከሰሱበት መሠረት “ጥፋተኛ” ሆነው እንዳገኛቸው አስታውቋል፡፡ ይኽ ዓይን ያወጣና ሕዝብን በእጅጉ የናቀ ብይን በማንም ላይ ሳይሆን በፍትኅ ላይ የተወሰደ፥ አቅጣጫ የሳተና በሁሉም ዘንድ ሊወገዝ የሚገባው መዘዘ-ብዙ አድራጎት ሲሆን በአገራችን ከግንቦቱ ቅልበሳ ጀምሮ የሽብርተኞች አገዛዝ እየተተከለ መሆኑን ገና ከጧቱ ሲያስጠነቅቅ ለቆየው ኢዴኃኅ ምንም የሚያስገርም አይደለም፡፡

እንዲህ ዓይነቱን የዕብሪት ድርጊት በዴሞክራሲያዊነት ታምተው ከማያውቁት የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች የሚጠበቅ ቢሆንም ትልቅ ስህተት የሚሆነውና ቀጣይ ትግላችንን የአቀበት ጉዞ ሊያደርገው የሚችለው ድርጊቱን ከማንኛውም ፀረ-ዴሞክራሲ ኃይል እንደሚጠበቅ አዘቦታዊ የአፈና እርምጃ አድርጎ መቁጠር ይመስለናል፡፡ ደግመን ደጋግመን እንዳልነው ከሁለት ዓመት ወዲህ ያለንበት አስከፊ የሆነ የቅልበሳ ሂደት ነው፡፡ በቅድመ-ግንቦት ወቅት በአገራችን የነበረው ዴሞክራሲ ገና በእንጭጭ ደረጃ የነበረ ቢሆንም የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች በነበሩበት የኪሳራ ደረጃ የኢትዮጵያ ሕዝብ ' የተሟላ ዴሞክራሲ' ሳያስፈልገው በነበረችው የዴሞክራሲ ጭላንጭል ተጠቅሞ በማያወላዳ ሁኔታ ታሪካዊ የሆነ ድል ለመጎናጸፍ በቅቷል፡፡ ገዥው ፓርቲና የነገው ሳይሆን የዛሬው ብቻ የሚታያቸው፥ ሰብዓዊነትም ይሁን ብሔራዊ ስሜት የለሾቹ መሪዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰጠውን የተስፋና የአንድነት ድምፅ በአደባባይ መስረቅ አልበቃቸውም፡፡ አሸባሪዎቹ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ከዚህ ሽንፈት የበኩላቸውን ትምህርት ቀስመዋል፡፡ ገና በእንጭጩ የነበረው ዴሞክራሲ ያደረሰባቸውን ከፍተኛ ኪሳራ በደንብ ስለሚያውቁት ከእንግዲህ እነኝህ ቀልባሾች በሕዝብ ትግል እንዲያፈገፍጉና እንዲንበረከኩ ከመገደዳቸው በፊት ተጨማሪ ዴሞክራሲ ቀርቶ የቅድመ-ግንቦቱ ሁኔታ እንኳን የሚመለስበት ምንም ተዓምር አይኖርም፡፡ ከዚህ ይልቅ በግልጽ እየታየ ያለው አካሄዳቸው ድምፁን በነፈጋቸው ምልዓተ-ሕዝብ ላይ በቀል የተቀላቀለበት የሽብር እርምጃ በመውሰድ ባለፉት አሥራ-አምስት ዓመታት ቀስ በቀስ ታጋይ ዜጎች እየሞቱ፥ እየታሰሩ፥ እየተሰደዱና እየተዋከቡ የገነቧቸውንና ፀረ-ሕዝብ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችን ለግንቦት ሽንፈት የዳረጓቸውን ውሱን የነበሩትን ዴሞክራሲያዊ ተቋማትና በጎ የፖለቲካና የሥነ-ልቦና ግኝቶች እንዳልነበሩ አድርጎ የማውደም ሙከራ ነው፡፡

ከዚህ ሂደት እኛ የኢትዮጵያ አገር-ወዳዶችና ዴሞክራቶች የግድ መቅሰም የሚገባን ትምህርት አለ፡፡ የቅልበሳውን አሳሳቢነት በመካድ፥ ቀልባሾቹ ያላቸውን ቁርጠኝነት በመናቅ 'ቀጣይ ምርጫ'፥ 'የፓርላማ ትግል'፥ ትርጉም በሌለው 'ድርድር' ስም በባዕዳን ሽምግልና

ከሕዝብ ጀርባ መመሳጠር፥ ከዴሞክራሲ ድል በፊት 'ብሔራዊ እርቅ'፥ ወዘተ.... በሚሉ መሥመር የሳቱ አስተሳሰቦች ከመነሁለል ይልቅ እነዚህ ለቅልበሳውና ለቀልባሾቹ ጊዜ ከመስጠት ሌላ ምንም የማይፈይዱ ጥቅመ-ቢስ ልፈፋዎች እንደሆኑ ተገንዝበን የግንቦትን ድሎች ለማስመለስና በነሱ ላይ ለመገንባት በቁርጠኛ የጋራ ትግል ላይ መሠማራት ይኖርብናል። ይኸንን ስናደርግ ደግሞ ከወዲሁ አንድ ቁም ነገር ከግንዛቤ ውስጥ አስገብተን መሆን ይኖርበታል። ይኸ ትግላችን የአቀበት ጉዞና ፍሬ-ቢስ እንዳይሆን ከፈለግን ዛሬ ስላለንበት ሁኔታ ግልጥልጥ ያለ ሥዕል እንዲኖረን ያስፈልጋል። ዛሬ ባለው ሁኔታ በተቃዋሚዎች ጎራ በትግሉ ላይ የደረሰውን የቅልበሳ ጥልቀት፥ ስፋት፥ መጠንና የመዘዙን አደገኛነት በቅጡ ያለመረዳት አባዜ በግልፅ እየታየ ነው። ግንቦት በአሥራ-አራት ዓመታት የግፍ አገዛዛቸው ታሪክ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ወደ ተከላካይነት ወርደው በፖለቲካው መስክ ሙሉ በሙሉ ተሸንፈው በሽብር ጎዳና እንዲሰማሩ የተገደዱበት እኛና ሕዝባችን ደግሞ ወደማያወላዳ የፖለቲካ የበላይነትና አጥቂነት ደረጃ የተሸጋገርንበት ሂደት ነበር። እራሳችንን እናታልል ካላልን በስተቀር ዛሬ ያለው ሥዕል የተገላቢጦሽ ነው። ሽብርና የአመራር ክፍተት ተጋግዘው በኅብረተሰባችን ዘንድ ጨለምተኝነትና ግራ መጋባት እንዲሰፍኑ፥ ሕዝባችን ለጊዜውም ቢሆን የትግል ትጥቁን እንዲፈታ ሁለንተናዊ የአፈና ውርጅብኝ እየደረሰበት እነሱ ወደ አጥቂነት እኛ ደግሞ ወደ ተከላካይነትና አቅጣጫ የመሳት አዝማሚያ ወርደናል።

የግንቦት ማግስት "የሕዝብ ድምፅ ይከበር" ብለን ተነስተን ሕዝባችንም ይችን ግልጽና ቀጭን ወቅታዊ መፈክር አንግቦ ሲተናነቅ አይከፍሉ መስዋዕትነት የተከፈለበት የትግል ወቅት ነበር። የተከላካይነት ምልክቱ ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ የዚህን ሕዝባዊ አጀንዳና መፈክር ወቅታዊነት ጥያቄ ውስጥ እያገቡ የሚሄዱ ኃይሎች ብቅ ማለት መጀመራቸው ነው። በግንቦት ማግስት ትግሉ የሚመራው አጥቂዎቹ እኛና ሕዝባችን በምናነሳቸው አጀንዳዎች ዙሪያ ነበር። የተከላካይነታችን ምልክቱ ዛሬ ባሻቸው፥ እንዳሻቸውና ያዋጣናል እያሉ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች በሚያስይዙንና በሚያስለቅቁን የቤት ሥራዎች ዙሪያ ከአጀንዳ አጀንዳ የምንከራተትበት አሳፋሪ ሂደት ውስጥ መሆናችን ነው። የተከላካይነታችን ምልክቱ በየጊዜው አጀንዳ ሲያስጨብጡን "ዛሬ ዋናው አጣዳፊ ተጋድሎ" ይኸ ነው ያ ነው እያልን ትግላችንንና ከአገዛዙ ጋር ያለንን መሠረታዊ የልዩነታችንን መነሾ ማለትም "መስመር የሳተው የዴሞክራሲ ሂደት መልሶ በእግሩ እንዲቆም" ብለን ከማካሄድ ይልቅ በየጊዜሠ "አጣዳፊ" ጉዳይ እየተከሰተ ይኸንን መሠረታዊ አጀንዳችንን "ለጊዜው" በይደር የማስቀመጥ አባዜ ነው። ያኔ በግንቦት ማግስት ትግላችን ሁሉም 'ያገባኛል' ብሎ በነቂስ፥ በጋራና በትግግዝ መንፈስ የሚያካሂደው ሕዝባዊ ተጋድሎ ነበር። የተከላካይነታችን ምልክቱ ዛሬ ይኸን የግንቦት መንፈስ መንከባከብ ትተን በተናጠል አጀንዳ የተናጠል ትግል እናካሂዳለን እየተባለ የሚደረገው አጓጉልና አጥፊ መግደርደር ነው።
ይኸ ማለት የታሰሩት ይፈቱ፥ የፕረስ ነፃነት ይኑር፥ ወዘተ.. እያልን የምናካሂደው የትግል አጀንዳችንን እንተው ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል። ይኸ ተጋድሎ አገራዊ፥ ሕዝባዊ፥ ሰብዓዊ፥ ሞራላዊና የተቀደሰ ተጋድሎ በመሆኑ መቀጠል ብቻ ሳይሆን መፋፋም ይኖርበታል። በደንብ ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ግን የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ተናጠል አጀንዳ የላቸውም። በጅምላ ሲያስሩም ሆነ አንድ ንፁህ ዜጋ በግፍ ሲረሽኑ፥ ፍርደ-ገምድል ብያኔ ሲያወርዱም ሆነ ከጠባብ ጠባብ የምንላቸው ጎጠኞች "በዓለም-አቀፉ ፀረ-ሽብር ትግል" በአሳፋሪ ቅጥረኝነት ተሰልፈው በአገራችን ደኅንነትም ሆነ ብሔራዊ ክብር ሲነግዱ ከነዚህ አንደኛቸውም ተናጠል አጀንዳ አይደሉም። ሁሉም የአንድ አጠቃላይ የሆነ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ኢትዮጵያስ አጀንዳ የማይነጣጠሉ አካላት ናቸው። እኛም ከዚህ ሌላ አካሄድ ሊኖረን አይችልም። ከእንግዲህ የዝቅተኛ ዝቅተኛ ሊባል የሚችል የመብት አጀንዳ የአጠቃላዩ አገራዊና ዴሞክራሲያዊ ትግላችን የማይነጠል አካል እንደሆነ ተገንዝበን የጋራ ትግሉን በዚህ መንፈስ ማካሄድ ይኖርብናል።

ዛሬ ሽብርተኞቹ ባሉበት የኪሳራ ደረጃ ትንሽ ይሁን ትልቅ ማንኛውም የትግል አጀንዳን እውን እንዲሆን ከባድ መስዋዕትነትን ሊጠይቅ የሚችል ሰፊ ሕዝባዊ ተጋድሎ

ማድረግና የአገዛዙ መሪዎች ከያዙት የጥፋት ሂደት እንዲያፈገፍጉ ማስገደድ ይኖርብናል። ትግላችን ፀረ-ሕዝብና አሸባሪዎቹን የማፈግፈግ ደረጃ ካደረሳቸው ደግሞ የሕዝባችን ትግል ወደ አጥቂነት እነሱ ወደ ተከላካይነት ይሸጋገራሉና ያ አዲስ የኃይል ሚዛን በዴሞክራሲና በሕዝባዊ ድል ሳይቋጠር የሚቆምበት ምንም ሁኔታ አይኖርም። ኅብረታችን በአንድ ሂዴት የግንቦትን ድሎች ለማስከበርና በነሱ ላይ ለመገንባት እንዋደቅ እያለ በተደጋጋሚ ጥሪ ሲያደርግ የቆየው ከዚህ ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ በመነሳት ነው። ለዚህ ሕዝባዊ አጀንዳ እውን መሆን እንዋደቅ ብለን ከተነሳን ደግሞ ይኸ የሚሊዮኖችን ድል የማስመለሱ ጉዳይ የሚሊዮኖችን ተጋድሎ ይጠይቃል በማለት ሰፊና ዘርፈ-ብዙ ትግል መካሄድ ይኖርበታል እያለን ሳናሰልስ ስንወተውት የቆየነው። ለዚህ ነው ሕዝባዊ ትግል ብለን ከተነሳን እነዚህን ሚሊዮኖች እንደ አንድ ሰው ሆናችሁ በኔ ሥር ተሰለፉ ሳይል የዚህ ሁሉን-አቀፍ ተጋድሎ አመራር ከፖለቲካ ድርጅርቶች እጅግ አልፎ የሚሄድ ሁሉን-አቀፍ አመራር እንደሚያስፈልገው በማመን በተደጋጋሚ ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ ተጠርቶ ለጋራ ትግል የጋራ ስትራቴጂ ይነደፍ፥ ለዚህ ስትራቴጂ ተግባራዊ መሆን ሁሉን-አቀፍ የሆነ የጋራ አመራር ይፈጠር እያልን ተደጋጋሚ ጥሪ ያደረግነው።

በአገራችን ያለው ሁኔታ እንዲሁ ይቀየራል ብሎ ማሰብ ይሁን ከዚህ አሸባሪ አገዛዝ ዴሞክራሲ ይፈልቃል ብሎ መጠበቅ ከእባብ እንቁላል እርግብ ይወለዳል ብሎ መጠበቅ ይሆናልና እጅ አጥፎ መቀመጡ የማይታሰብ ጉዳይ ነው። የዚያኑ ያኸል ደግሞ በሰከነ ሁኔታ ተመክሮበትና የጋራ የሆነ የአጭርና የረጅም ጊዜ ስትራቴጂና ስልት ተነድፎ ትግሉን በጋራ ለማካሄድ እምነት ላይ የተመሠረተ የጋራ አሰላለፍ እስከሌለ ድረስ በተናጠል አጀንዳ በተናጠል ድርጅታዊ ጥሪ፥ በስንጥር ጉዞ፥ በተናጠል ትግልና በግብታዊነት የሚሞከር አካሄድ የሽብርተኞቹን ደንታ-ቢስነትና ቁርጠኝነት ከስሌት ውስጥ ያላስገባና ሕዝባችንን በተለይም ወጣቱን ለአላስፈላጊና ፍሬ-ቢስ መስዋዕትነት የሚጋብዝ ጥሪም እንዲሁ ከጥያቄ ውጭ መሆን ይኖርበታል። ከዚህ ይልቅ ከቡድነኛነትና ከጠባብ ድርጅታዊ አስተሳሰብ ወጥቶ ትግሉን አስፍቶና አርቆ ባየ የጋራ አሰላለፍ በቀናና በቁርጠኛ የግንቦት የአንድነት መንፈስ መያያዝ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው እንላለን።

ዛሬ ሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም በተለይ በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ መሪዎችና በሌሎች ንፁኃን ዜጎች ላይ የተሰጠውን የፖለቲካ ብይን ኢዴኃኅ አጥብቆ ያወግዛል። ይኸ ፍርደ-ገምድል የፖለቲካ ብይን በአንድ ድርጅት ወይም ተቋም ላይ የተሰነዘረ ሳይሆን በአጠቃላይ ለአገዛዙ ቁንጮዎች እርም በሆኑባቸውና በሚያንገፈግፏቸው በኢትዮጵያዊነትና በፍትኅ ላይ ስለሆነ መፍትኄው ሁሉን-አቀፍ የሆነ ወሳኝ የጋራ ትግል ማድረግ ብቻ ነው።

ስለሆነም ኅብረታችን በተለይ ከድኅረ-ምርጫ ዘጠና ሰባት ጀምሮ ያለማቋረጥ ሲወተውት እንደቆየው ሁሉ አሁንም አገዛዙ ላይ አስገዳጅነት ያለው የተቀናበረ ትግል ለማድረግ እንዲቻል የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት፥ ስብስቦችና አገር-ወዳዶች የሚካፈሉበት የምክክር ስብሰባ በአስቸኳይ እንዲጠራ እነሆ በድጋሜ በአክብሮት እናሳስባለን።

ፍትኅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ!
ድል በተባበረ የሕዝብ ትግል!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት
ሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም

---

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132